የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ–ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 59
ADDIS ABABA–22nd May, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የናርኮቲክ ዕፆችና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ዓለም አቀፋዊ ሕገወጥ ዝውውር፣ የዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትና የተደራጁ ወንጀሎችን ለመከላከል የተፈረመው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፪ሺ፩፻፹፮

## CONTENTS

Proclamation No. 339/2003
Cooperation Agreement with Republic of Turkey in Fighting Against International Illicit Trafficking in Narcotic Drug and Psychotropic Substances, International Terrorism and Organized Crime Ratification Proclamation ........................ Page 2186

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፱/፲፱፻፺፭
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በቱርክና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ወዳጅነትና ትብብርን ለማስፋፋት የሚያስችሉ መሠረታ ስምምነቶችን ከቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተፈረመ በመሆኑ ፤

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ መስኮች የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ትብብርን ለማስፋፋት ያለውን ፈቃደኝነት በተደ ጋጋሚ የገለጸ በመሆኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የናርኮቲክ ዕጾችና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ዓለም አቀፋዊ ሕገወጥ ዝውውር ፣ የዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትና የተደራጁ ወንጀሎችን ለመከላከል የተፈረመው ስምምነት ለማጽደቅ የወሰነ በመሆኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የናርኮቲክ ዕጾችና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ዓለም አቀፋዊ ሕገወጥ ዝውውር ፣ የዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትና የተደራጁ ወንጀሎችን ለመከላከል የተፈረመው ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፱/፲፱፻፺፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION No. 339/2003
### A PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF COOPERATION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKEY

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has entered into basic Agreement with the Government of the Turkey for the promotion of friendly relations and cooperation among the people of the two countries;

WHEREAS, the Government of Ethiopia has expressed its willingness to develop cooperation's in various fields in conformity with mutual benefits;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the ratification of the Cooperation Agreement Between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey in fighting Against International Illicit Trafficking in Narcotic Drugs and Psychotropic Substances, International Terrorism and Organized Crime signed in Addis Ababa on 28th of March, 2001, at its session held on 22nd day of May, 2003.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Cooperation Agreement with Republic of Turkey in Fighting Against International Illicit Trafficking in Narcotic Drugs and Psychotropic Substances, International Terrorism and Organized Crime Ratification Proclamation No. 339/2003"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱን ስለማጽደቅ</u>

መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የናርኮቲክ ዕጾችና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ዓለም አቀፋዊ ሕገወጥ ዝውውር ፣ የዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትና የተደራጁ ወንጀሎችን ለመከላከል የተፈረመው ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በዚህ አዋጅ አጽድቋል ።

፫· <u>የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Cooperation agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Turkey in Fighting Against International Illicit Trafficking in Narcotic Drugs and Psychotropic Substances International Terrorism and Organized Crime signed on 20th March, 2001, is hereby ratified by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3. *Power of the Minister of Federal Affairs*

The Minister of Federal Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of 22nd day of May, 2003.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of May, 2003

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE